**ፕሬስ ሪሊዝ**
ህዳር 09 ቀን 2000 ዓ.ም
**ማስታወቂያ ሚኒስቴር**

## ሞቃዲሾን ከሽብርተኞች ለማጽዳት እየተደረገ ላለው እንቅስቃሴ ውጤታማነት የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ አፋጣኝ ድጋፍ ወሳኝ ነው

በእስላማዊ ፍርድ ቤቶች ኅብረት የሚደገፈው የአልሸባብ ሽብርተኛ ቡድን ርዝራዦች ባለፉት ጥቂት ሣምንታት በዋናነት በሞቃዲሾ ከተማ የከፈቱትን የሽብር ጥቃት ለማምከን የሶማሊያ የሽግግር መንግሥት ወታደሮች፣ የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊትና ኅብረተሰቡ በጋራ ሲንቀሳቀሱ እንደነበር ይታወሳል፡፡

በዚህ ሽብርተኞችን ከመኖሪያ አካባቢዎችና ከኅብረተሰቡ በመለየት የመመንጠርና ከተማዋን የማረጋጋት ሥራ ተጠናክሮ በቀጠለበት ሁኔታ ሽብርተኞች ባካራ በሚባለው የገበያ አካባቢ ብቻ እንዲሰባሰቡ የተገደዱበት ሁኔታ ተፈጥሮ ቆይቷል፡፡ ከተማዋንና በዋናነትም የመኖሪያ አካባቢዎችን ከሽብርተኞች የማጽዳት እንቅስቃሴ በከፍተኛ ጥንቃቄና ስልት እየተካሄደ በነበረበት ሁኔታም ሽብርተኞች በተስፋ መቁረጥ ስሜት ንፁሀን ዜጎችን ለከፍተኛ ጉዳት የዳረጉ ጥቃቶችን ፈጽመዋል፡፡

የሶማሊያ የሽግግር መንግሥት እና የኢትዮጵያ የመከላከያ ኃይሎች ከሰላም ወዳድ የከተማው ኗሪዎች፣ የጎሳ መሪዎችና አባላት ባገኙት ሙሉ ድጋፍ በመታገዝ በወሰዱት ሽብርተኞችን የመደምሰስ እርምጃ ካለፉት ጥቂት ቀናት ወዲህ በከተማዋ መረጋጋትን መፍጠር ተችሏል፡፡ ይህ አሁን በከፍተኛ ትግልና መስዋዕትነት እየሰፈነ የመጣውን ሰላም በዘላቂነት ለማስቀጠልም የሽግግር መንግሥቱና ኅብረተሰቡ በጋራ እየተንቀሳቀሱ ይገኛል፡፡ ከተማዋ አንፃራዊ ሰላም ማግኘቷንም የሽግግር መንግሥቱ ከፍተኛ ባለሥልጣናት በሰጡት መግለጫ አረጋግጠዋል፡፡ ሰላም ወዳድ የከተማዋ ኗሪዎች፣ የጎሳ መሪዎችና የኅብረተሰብ አባላትም ሽብርተኞችን በማውገዝና

ከሽግግር መንግሥቱ ጎን እንደሚቆሙ ያላቸውን ቁርጠኝነት በሰላማዊ ሰልፍ አረጋግጠዋል፡፡

ይህ አሁን እየታዬ ያለው መረጋጋትና ሰላም የሚያመለክተው ነገር ቢኖር በከተማዋ ለሚፈጠር ማንኛውም ሁከት ብቸኛው መንስዔ የሽብርተኞች ፀረ-ሰላም እንቅስቃሴ ብቻ እንደሆነ ነው፡፡ ይህም የሽብርተኞችን እንቅስቃሴ ሙሉ ለሙሉ መቆጣጠር ከተቻለ የሶማሊያን ሰላምና መረጋጋት በአጭር ጊዜ ውስጥ እውን ማድረግ እንደሚቻል በግልጽ ያመለክታል፡፡

በመላ ሶማሊያ በተለይም በሞቃዲሾ ዘላቂ ሰላምን ከማረጋገጥና ሕጋዊው የሽግግር መንግሥት እንደመንግሥት ሀገሪቱን እንዲመራ ለማድረግ የሚደረገውን ጥረት ለማገዝ የተባበሩት መንግሥታትና የአፍሪካ ሕብረት እንዲሁም የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ በጋራ መንቀሳቀስ ይኖርባቸዋል፡፡ በሶማሊያ የሰላም አስከባሪ ኃይል ለማስፈር የወጣው እቅድም በአፋጣኝ ተግባራዊ መደረግ ይኖርበታል፡፡ በዚህ ረገድም ዑጋንዳ የወሰደችው ቀዳሚ እርምጃ አርአያነት ያለውና የሚደገፍ ነው፡፡ የዑጋንዳ ሰላም አስከባሪ ኃይሎች በሽብርተኞች ዛቻና አልፎ አልፎ በሚሰነዝሩት የቀቢፀ ተስፋ ትንኮሳ ሳይደናገጡ ለዓላማቸው በጽናት ቆመው የሚፈለግባቸውን አስተዋጽኦ እያደረጉ መሆኑ ከፍተኛ አድናቆት የሚቸረው ነው፡፡

ይህን መሰል ጥረት ለማገዝም ናይጄሪያ በቅርቡ የሰላም አስከባሪ ኃይል ወደቦታው ለመላክ ዝግጅትን ማጠናቀቋ መግለጹ የሚደነቅ ነው፡፡ ይህ እርምጃም የሰላም አስከባሪ ኃይል ወደ ስፍራው ለመላክ የተስማሙ ሌሎች ሀገራትና ጥረቱን በገንዘብ የሚደግፉ አካላት ይህንን አርአያ እንዲከተሉና ቃላቸውን አክብረው እንዲገኙ ጥሪ የሚያስተላልፍ በጎ ጅምር እንደሆነ ይታመናል፡፡ የአፍሪካ ኅብረት የሽግግር መንግሥቱን በመደገፍ በሶማሊያ ዘላቂ ሰላምን ለማረጋገጥ ከመነሻው ጀምሮ የያዘውን ቁርጠኛ አቋም አጠናክሮ በመቀጠል ሶማሊያ እንደመንግሥት ተቋቁማ ሰላሟንና ልማቷን ለማፋጠን የሚያስችል ሁኔታ እንዲፈጠር ለማድረግ በተባበሩት መንግሥታት፣ በአውሮፓ ኅብረት፣ በአረብ ሊግና ሌሎች አግባብ ባላቸው ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ሊደገፍ ይገባል፡፡

በዚህ ረገድም ኢትዮጵያ በሶማሊያና ብሎም በአፍሪካ ቀንድ ዘላቂ ሰላምን ለማስፈንና የሀገራትንና የሕዝቦችን የጋራ ትብብርና መቀራረብ ለመፍጠር እስካሁን እያደረገችው ያለውን ገንቢ አስተዋጽኦ አጠናክራ እንደምትቀጥል ታረጋግጣለች፡፡ ሽብርተኞችን ነጥሎ የመደምሰስና እንቅስቃሴአቸውን የማምከን ጥረት በሰላም ወዳድ የሶማሊያ ሕዝብ ቀጥተኛ ተሳትፎና በዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ድጋፍ ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡

# # # #